# አዲስ ዘመንና -አዲስ ነገር

ደረጀ ሀብተወልድ( ሆላንድ)

**መቅደስ እንሥራ አለን-መቅደስ አብረን ሠራን -መሰዊያው ታደሰ፣**

**ቄስ አድርጉኝ አለን፣ይሁንታ ሰጠነው፣ ሳይደቁን ቀሰሰ፣**

**ነቢይ ሳይቀባው-የዘይቱን ብልቃጥ-በራሱ አፈሰሰ፣**

**በራሱ ነገሰ፣**

**“ነፃነት፤መቻቻል፤ፍትህ “ በሚል ፅህፈት-ክንዱን ተነቀሰ፣**

**ሆኖም ምን ያደርጋል......?**

**“እኛን ያልመሰለ-“ውጉዝ ከመ አርዮስ!!!” እያለ ቀደሰ።**

**{ጋዜጠኛው ፡-ከሚለው የራሴ ግጥም}**

በይዘቱ ሳይሆን በኪሎው {በክብደቱ}የሳንቲም ዋጋ የሚያወጣው አዲስ ዘመን፤ከመንታ ወንድሙ ከኢቲቪ ጋር በመተጋገዝ የግሉ ፕሬስ ላይ “ፖለቲካዊ እርምጃ” ሊያስወስዱ መዳከር ከጀመሩ ሰንበትበት አሉ። ልብ በሉ አዲስ ዘመንና ኢቲቪ ናቸው በግሉ ፕሬስ ላይ እየዘመቱ ያሉት።አሁንም እደግመዋለሁ እንዳትስቁ -አዲስ ዘመንና ኢቲቪ ናቸው ለጋዜጠኝነት ሙያ ጠበቃ ነን እያሉ ያሉት ።” ኢቲቪና አዲስ ዘመን -በአዲስ ነገር፣በነፃነት፣ በሀዳር፣ በአዲስ ዜና፣ በምኒልክ፣ በአባይ ወዘተ ላይ ዘመቱ፤ወንዞች ሽቅብ ፈሰሱ።እዚህ ላይ ምነው ከተቋቋሙ አያሌ ዘመናት ያሳለፉትን አንጋፋ ተቋማት ፤ብዙ እድሜ ከሌላቸው ጋዜጦች አሳነስካቸው የሚል ካለ፡-

መልሕቅ አርባ ዓመት ውሀ ውስጥ በኖረ፣

ተዘፈዘፈ እንጅ መች ዋና ተማረ? ነው መልሱ።

አዎ! በሀይለስላሴ ዘመን “ንጉሱ ተኙና ተነሱ” በሚል ዜና ስራቸውን ያሟሹትና ዛሬም ከረዥም ዓመታት በሁዋላ፡-”ፕሬዚዳንቱ ችግኝ ተከሉ”ከማለት ብዙም ጋት መራመድ ያልቻሉት አዲስ ዘመንና ኢቲቪ፤”በነዛ አገሮች በግል ፕሬስ ስራ መሰማራት በፈንጅ ላይ እንደመራመድ ይቈጠራል”ከተባለላቸው አገሮች አንዷና ዋነኛዋ በሆነችው ኢትዮጵያ ውስጥ ከነችግራቸውም ቢሆን ሀቅን እየተጋፈጡ ያሉ ጋዜጦችን ለመተቸት የሚያስችል ምን ሙያዊስ ሆነ ሞራላዊ ብቃት አላቸው?አገር ውሰጥ ገቢ ሌላ ስራ ያለው ይመስል ግብር መሰብሰቡን ዜና እያለ የሚነግረኝ ኢቲቪ፤ስለ ዜና ምንነት ላስተምርህ የሚለኝ በምን ሂሳብ ነው?ሰላማዊ ሰልፈኞች በጥይት በተመቱ ማግስት በወቅታዊ አምዱ ስር “ጨውና ጥቅሙ” የሚል ፅሁፍ የለጠፈው አዲስ ዘመን፤ ‘ ስለሚዛናዊነት ፤fact’፤ ወቅታዊነት፤ ቀጥተኛነት፤ድፍረትና ለእውነት መሰጠት ስለመሳሰሉት የጋዜጠኝነት ተግዳሮቶች{ Challenges} ልናገር የሚለው በማን ሜትር ነው?

በኢትዮጵያ የግል ፕሬሱ ካለው አጭር ታሪክ አኳያ እዚህና እዚያ ስህተት መፈጠራቸው የሚካድ አይደለም። በአፈና ስርአት ውስጥ ያለፈ ህብረተሰብ በጥቂቱም ብትሆን ገርበብ ያለች በር ስትከፈትለት ሊፈጠር የሚችለው ዓይነት ችግር በፕሬሱም ላይ ሊታይ ሂደቱ ግድ ይላል። ምክንያቱም በፕሬሱ ስራ የተሰማሩት ጋዜጠኞችም የዚሁ ህብረተሰብ አብራክ ክፋዮች እንጅ ከሌላ ፕላኔት የመጡ ፍጡራን አይደሉም።እንደውም በዲሞክራሲ በዳበሩት አገሮች የሚገኙት ፕሬሶች ካለፉበት ሂደት አኳያ ነገሩን ካስተዋልነው፤የ ኢትዮጵያ የግል ፕሬሶች በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ የሰሩት ስራም ሆነ የደረሱበት ደረጃ ይበል የሚያሰኝ ነው።

“የደረሱበት ደረጃ” የሚለው አገላለፅ በዘርፉ ሙያዊ እድገት መታየቱን ለማመላከት የተጠቀምኩበት ሀረግ ነው።አዎ! የነ አቶ በረከትን ሚዛናዊነት የጎደለው ወይም ፖለቲካዊ ወገንተኝነት የተንፀባረቀበት አስተያዬት ተከትሎ ሰሞኑን በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በግሉ ፕሬስ ዙሪያ የተሰራው ጥቁር ፕሮፓጋንዳ ውሀ ሊያነሳ የማይችለው፤ በአይናችን

ያየነውን የቅርብ ጊዜ ሀቅ ጥላሸት ሊቀባ በመሞከሩ ነው።በተለይ በምርጫ 97 ሰሞን ይታተሙ ስለነበሩት ፅሁፎች በተደጋጋሚ እየተስተጋባ ያለው ባዶ ጩኸት ጉንጭ ከማልፋት ውጭ የነበረውን ታሪካዊ ሀቅ አይቀይረውም። በወቅቱ ይታተሙ ከነበሩት ጋዜጦች ብዙዎቹ እንዲታሸጉ፤ አንዳንዶቹ ለጊዜው እንዲቆሙ የተደረጉት ፤ከ 80ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ እስከ ምርጫው ዋዜማ ድረስ ሲታተሙ ከነበሩት ፅሁፎች የተለዩ ስህተት ስለፃፉ እንዳልሆነ በየዓዳችን የሚገኙት እነዛው ጋዜጦች ህያው ምስክሮች ናቸው። ይልቁንም በኢትዮጵያ ፕሬስ ታሪክ እንደ ነፃነት ያሉት ጋዜጦች ከ100 ሽህ ኮፒ በላይ መሸጥ በመጀመራቸውና ለገዥው ፓርቲ ስልጣን ስጋት ስለመሰሉ ተዘግተዋል፤ጋዜጠኞቹም ታስረዋል ቢባል ሚዛን ይደፋል።*(ሲሉ ሰምታ ... እንዲሉ በወቅቱ የግል ፕሬሶችን የህትመት ብዛት የተመለከቱት የአዲስ ዘመን ሀላፊዎች "ከማን አንሼ..." በሚመስል ሀሳብ በግንቦት 20፣ 1997 ዓ.ም እለት አዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወትሮው በተለየ መ ልኩ በርካታ ገፆችን ይዞ በባለቀለም ህትመት 100 ሺህ ኮፒ እንዲታተም ቢያደርጉም ፤ ሩብ የሚያህለው እንኳ ሊሸጥ ባለመቻሉ በሚቀጥሉት ቀናት ከአዟሪዎች እቅፍ ተሰብስቦና በአይሱዙ መኪናዎች ተጭኖ መርካቶ ውስጥ ለመጠቅለያ በኪሎ መሸጡን ይህ ፀሀፊ ያውቃል ብቻ ሳይሆን፤" አዲስ ዘመን በኪሎ እየተቸበቸበ ነው" በሚል ርእስ ክስተቱን ይሰራበት በነበረው ጋዜጣ የወግ አምድ ስር አሰፍሮታል*)

እንዴ! የግሉ ፕሬስ ጋዜጠኞች ከቅንጅት መሪዎች ጋር በተከሰሱበት ጊዜ የቀረቡባቸው ማስረጃዎች እኮ በርዕሰ አንቀፆቻቸው "ብሄራዊ የአንድነት መንግስት ይቋቋም!" በማለት የቅንጅትን አቋም አራምደዋል "እየተባሉ ነው። በወቅቱ የነበረውን የፖለቲካ ትኩሳትና ጡዘት የተመለከተ ጋዜጠኛ ፤"የሚያዋጣን ብሄራዊ መግባባትና የአንድነት መንግስት ነው" ብሎ መፃፉ ህገ-መንግስትን መናድና የአገር ክህደት የሚሆነው በነማን መነፅር ነው? ብሄራዊ መግባባትና የአንድነት መንግስት የሚለውንስ ሃሳብ የቅንጅት ብቻ ማን አረገው? ይህኮ ከኢህአዴግ አመራሮች በስተቀር የብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ ፍላጎትና ምኞት ነው።እናም እደግመዋለሁ የወቅቱ ፕሬሶች የህጋዊ እርምጃ ሰለባ የሆኑት እንደሚባለው የተጋነነ ጥፋት ስለፈፀሙ ሳይሆን ሰፊ ተቀባይነት ስላገኙ ነው ቢባል ያስኬዳል።

እንደውም በግሉ ፕሬስ ታሪክ የመረጃ እጥረት የተቀረፈበት ጊዜ ቢኖር ፤የምርጫ 97 ወቅት ነው።የወቅቱ የቅንጅት አመራሮች ምንም አይነት የተቋማት ምርጫ ሳያደርጉ ማለትም ሬዲዮ ፋናን፣ዋልታን፣ኢቲቪንና ኢፍቲን የተባለችውን የኢትዮ-ቻነል እናት ሳይቀር ሳይለዩ ለሁሉም የኢትዮጵያ ፕሬሶች በአማካይ በሳምንት አንድ ቀን ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠት በጀመሩበት ወቅት፤ የግሉን ፕሬስ ውሸት ለማተም የሚያስገድደው ጫና ስላልነበረ ፤ባብዛኛው በወቅቱ ጋዜጦች ላይ ውሸት እንዳልተፃፈ ኢህአዴጎችም ያልሳቱት ሀቅ ነው።

በኢንተር አፍሪካ ግሩፕ ተዘጋጅቶ ቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት ያገኘውን የፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክር የተመለከተው ህዝብ፤ ለጠማው ለውጥ በቅንጅት መሪዎች ላይ ተስፋውን ጣለ።የኢህአዴግ "ላም አለኝ በሰማይ ..." መሆኑን አውቆታልና ለአዲሶቹ ቃልና ተስፋ፤ ልቡን ሰጠ። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት አዲሶቹም የኢቲቪው ስርጭት የፈጠረላቸውን መልካም ገፅታ በመጠቀም በመረጃ ድርቀት ሲሰቃይ ለነበረው የህትመት ሚዲያው ዘርፍ ሳምንታዊ ሌማት በማዘጋጀትና ቃለ-ምልልስ በመስጠት ተስፋ ከጣለባቸው ህዝብ ጋር መገናኘቱን ቀጠሉ። ጠልቀው ገቡ። "እነሱ ገርበብ ያረጉትን- እኛ በርግደነው ገባን" ያለው ማን ነበር? በህዝብና በአመራሮች መሀል የድልድይነት ሚና መጫዎት ደግሞ የጋዜጠኝነት አይነተኛ ተልዕኮ ነውና ጋዜጦቹም ከጋዜጣዊ መግለጫዎቹ በተጓዳኝ የአመራሮቹን ቃለ ምልልሶች ማተማቸውን ቀጠሉ። ዶክተር ብርሀኑ ለቃለ-ምልልስ ፈቃደኛ በሆኑበት ፤ ኢንጂነር ሀይሉ መግለጫ የምሰጠው ለነ እገሌ ጋዜጦች ብቻ ነው ባላሉበት፤ አርቲስት ደበበ ለጋዜጠኞች በሩን ባልቆለፈበት ይልቁንም ሁሉም የወቅቱ አመራሮች፡-"ለጋዜጠኞች ቢሯችን ብቻ ሳይሆን ልባችንም ክፍት ነው" ባሉበት ሁኔታ፤ ፕሬሱን "በሬ ወለደ "ለመፃፍ የሚገፋፋው አንዳችም ምክንያት አልነበረም።በ 1997 ፤ የግል ፕሬሶቹ ከመንግስት አካላትና ተቋሟት የመረጃ እጥረት ስላጋጠማቸው ፤ቀደም ባሉት አመታት እንደነበሩት፤ማለትም አሁን የጋዜጠኛ ማህበር መሪ ነኝ የሚሉት አየር ወለዱ ግለሰብ( አገለባበጡ - ዕውነትም ኤር ቦርን ያሰኛል) ያሳትሙት እንደነበረውና ሂደቱ ከገበያ ጠርጎ እንዳስወጣው አንደነመይሳው ጋዜጣ ባዶ ወሬ አላተሙም ወይም አልዋሹም። ስለዚህ በወቅቱ ጋዜጦች ላይ "fact" የተሰኘው የጋዜጠኝነት ዋነኛ ሙያዊ ስነ-ምግባር አልተጣሰም ማለት ነው።በዚህ ከተስማማን እቀጥላለሁ፡-

እዚህ ላይ ብዙዎቹ ጋዜጦች ሚዛናዊስ ነበሩ ወይ? የሚል ጥያቄ መከተሉ ግድ ነው። ሚዛናዊነት በማን መለኪያ? የሚል ጥያቄ ሳናስከትል "አይደሉም" በሚለው እንስማማ እንበል።ከጋዜጠኝነት ስነ-ምግባሮች አንዱ ሚዛናዊነት እንደሚባል የጋዜጠኝነት ሀሁን የቆጠረ ሁሉ የማይስተው ቢሆንም፤ይህን ሙያዊ መርሆ አንፃራዊ በሆነ መልኩ

ካልሆነ በስተቀር በተሟላ ሁኔታ በነ ሲ.ኤን.ኤን እና ቢቢሲ ላይ እንኳ ለማየት ከመቋመጥ ፤እንደ ዲዮጋን ፋኖስ ይዞ እውነትን መፈለግ ይሻላል እየተባለ ነው።ሚዛናዊ አለመሆን ከሙያዊ መርሆው አኳያ ሞራላዊ ወቀሳ ያስከትል ካልሆነ በስተቀር በህግ ስለማያስጠይቅም ፤በዐለማችን ይህን መርሆ በመጣስ ፍርድ ቤት የቀረበ አንድም ጋዜጣና ጋዜጠኛ ስለመኖሩ ሰምተን አናውቅም-ልብ በሉ በዐለማችን እንጅ በአገራችን አላልኩም።ሆኖም፤ ከሳምንታት በፊት የአዲስ ነገር አዘጋጆች፡- ” አዲስ ነገር ጋዜጣ ሚዛናዊ አይደለችም”የሚል ርዕሰ- አንቀፅ በማተማቸው፤ ሰማዩ እንደ ናስ የተከነበለ ያህል በ“ዞምቢዎች” መንደር እሪታ መበርከቱን ታዝበናል። በመሆኑም በሀሳቡ ዙሪያ ገፍቶ መከራከር (ምናልባት ይህን ፅሁፍ አገር ቤት ያሉ ጋዜጦች ከኢንተርኔት ማግኘት ችለው ለማተም ከመረጡት)ዋይታና ግርግሩን ያባብሰዋል ብዬ ስለምሰጋ እዚሁ ላይ በእንጥልጥል ላልፈው እገደዳለሁ።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በአመዛኙ በግል ፕሬሶች ዘንድ ይታይ ለነበረው ሚዛናዊ ያልሆነ አዘጋገብ ስህተቱ የጋዜጠኞቹ ብቻ ነበር ወይ? እንዲሁም ስለ “ሚዛናዊነት” መርሆ መከበር እየተሟገቱ ያሉት ወገኖች በሚያስተዳድሯቸው ፕሬሶች ዘንድ የሚቀርቡት ዘገባዎች ከሚዛናዊነት አንፃር ሲቃኙ ምን ይመስላሉ? የሚሉት ጥያቄዎች በአጭሩ መመለስ አለባቸው።

ከአሳታሚዎቹና ከጋዜጠኞቹ ፍላጎቶች ባልተናነሰ {ሃሳባቸውን የማተም መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ} መልኩ በግል ፕሬሶች ላይ ለሚታየው የሚዛናዊነት ጉድለት መንግስት ራሱ ዋነኛ ተጠያቂ ነበር ወይም ነው።የግል ፕሬሶች ከመንግስት አካላት ወይም ተቋማት መረጃ ለማግኘት ከሚሞክሩ፤ በነዳጅ ቁፋሮ ላይ ቢሰማሩ ይመርጡ እንደነበር ራሳቸው መረጃ ሰጪዎቹ የሚያውቁት ሀቅ ነው።አዎ!የኢትዮጵያ የግል ፕሬሶች ስለ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ከአል-ሀያትና ከቢቢሲ እየጠቀሱ ሲዘግቡ መኖራቸውን ማን ይዘነጋዋል?ህዝባዊና መንግስታዊ መረጃዎች ብቻ ሳይሆኑ የቢሮዎች፣የፍርድ ቤቶች፣የፓርላማና የሌሎች መሰል ተቋማት በሮች ለግሉ ፕሬስ በብረት ቅርቃር በተከረቸሙበት ሁኔታ -“ፕሬሶቹ ሚዛናዊ አልነበሩም” ብሎ መክሰስ ምን የሚሉት ገታራ ፈሊጥ ነው? በወቅቱ አቶ መለስ ወይም አቶ በረከት ለአንድ ጊዜ ታህል እንኳ ሳት ብሏቸው የግሉን ፕሬስ ለጋዜጣዊ መግለጫ ጋብዘው ቢሆን ኖሮ፤ የሚዛናዊነት ጉድለቱ ክስ ትንሽ ውሀ ባነሳ ነበር። **ግን አላደረጉትም።እነሱ ይህን ባላደረጉበት ሁኔታ በግንቦት 97 አካባቢ የነበሩትን ጋዜጦች በሚዛናዊነት ለመክሰስ መሮጥ ፤በዐይኑ ስር ምሰሶ ተገትሮ ከወንድሙ አይን ጉድፍ ሊያወጣ እንደቸኮለው ግብዝ መሆን ነው።**

እንዲሁም ፤ዛሬ ኢህአዴግ ወይም መንግስት ከ97ቱ የቅንጅት አመራሮች ትምህርት በመውሰድ ወይም በራሱ ውሳኔ -በአቶ መለስ አማካይነት በአማካይ በየሁለት ወሩ የግሎቹን ጨምሮ ለአገር ውስጥ ጋዜጠኞች ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠት መጀመሩ፤ “ጨርሶ ከመቅረት መዘግዬት ይሻላል” የሚያሰኝ በጎ ጅምር ቢሆንም፤ “ ይችን መብት ስለሰጠናቸው ...ትን ሽ እናቅምሳቸው” በሚመስል መልኩ -ይህንኑ ተከትሎ ብቸኛውና ጉደኛው የቴሌቪዥን ጣቢያችን በዶክመንተሪ ስም በግሉ ፕሬስ ላይ ያሰራጨው “ቀረርቶ”፤ “ ፍየል ከመድረሷ ...” አለያም “ እርሟን ብታፈላ ጀበና ሁሉ አተላ” የሚያሰኝ ነው።

በጣም የሚያስቀው ደግሞ የግሉን ፕሬስ በሚዛናዊነት ጉድለት እየከሰሱ ያሉት፤ በዶክመንተሪ ስም - ዘገባ ያስተላለፉት ሳይሆን ጡሩምባ የነፉት እነዚሁ ሚዲያዎች መሆናቸው ነው።

አዎ!የግሉ ፕሬስ ሚዛን መጓደልና ከዲሞክራሲ መንገድ ጋር የመጣረስ ሁኔታ ከመስመር ወጣ በማለትና ወደ ጫፍ {extreme}በመሄድ ሊገለፅ ይችላል ይባል ይሆናል። ይህ ግን ቀደም ሲል እንደገለፅኩት ባደጉት አገሮች እንደሆነው ሁሉ የዲሞክራሲ ሂደት አንድ አካልና እያደር እየከሰመ የሚሄድ ነው። በአገራችንም መሻሻሉ እየታየ ነበር።እጅግ አስፈሪው፣ሊሻሻል ያልቻለውና ኢትዮጵያውያንን ለዘመናት እንደመርግ ተጭኖን ያለ ነገር ቢኖር፤ከግሉ ፕሬስ ተቃራኒ በሆነ መልኩ በመንግስት ሚዲያው በኩል በአፈና የሚገለፀው ኢ-ዲሞክራሲያዊነት ነው።ይባስ ብሎ እነዚህ በህዝብ ሀብት የሚተዳደሩ ሚዲያዎች የአንድ ፓርቲ ቀኖና ማስተጋቢያ ሆነው ሳለ ፤ግለሰቦች በራሳቸው ገንዘብ የሚያሳትሟቸውን ፕሬሶች በሚዛናዊነት ሲከሱ መስማቱ ደግሞ እጅግ ያሳፍራል፤ ያስፈራልም።

አዎ!የህዝብ ሀብት የሆኑ ሚዲያዎች ለዘመናት ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ሀሳቦችና አመለካከቶች ዝግ ሆነው- ወደ ስልጣን የሚወጣ ቡድንን ቀኖና ብቻ ሲያስተጋቡ ከመስማት የከፋ ኢዲሞክራሲያዊነት ወይም አገራዊ ህመም ምን አለ? ከዚህም ባሻገር እነዚህ ተቋማት የአየር ሰአታቸውን ፈቅደናል ባሉባቸው አንዳንድ ጊዜያትስ፤ የስንት ሰዎችንና ፓርቲዎችን ሀሳቦች፣መግለጫዎችና ቃለ-ምልልሶች በትክክል አስተላልፈዋል? ብለን ስንጠይቅ ደግሞ፤ የገዛ

አገራችንን እንፈራለን። በእርግጥም በኢዲቲንግ ስም ሆነ ብለው ሃሳብንና እውነትን ቆራርጠው ከሚያሰራጩ የብዙሀን መገናኛዎች በላይ ምን የሚያስፈራ ነገር አለ? እንዲሁ ሳስበው ከምፈራቸው ነገሮች አንዱ እባብ ነው፤ እውነት እውነት እላችሁዋለሁ፡-የምፈራው አውሬ ከሚተፋው መርዝ የበለጠ - እነዚህ ሚዲያዎች፤ በሀሳብ ስም የሚረጩት ዛቻ ያስፈራኛል።

ለመሆኑ ሰሞኑን ኢቲቪ የከፈተው ዘመቻ፤" በዶክመንተሪ" ስም ከመቅረቡ ውጭ - በምርጫ 97 ወቅት በግሉ ፕሬስ ላይ የማሸግና የማሰር እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ከተከፈተው ዘመቻ ጋር ልዩነቱ ምንድነው?ዛሬ አዲስ ነገሮች ዛቻውንና ክሱን- ሊወሰድባቸው ስለታቀደው እርምጃ እንደ አንድ ማስረጃ ሲያቀርቡ***፤"በሀሳብ ተሞገቱ እንጂ እነሱን ማሰር የመንግስት ሀሳብ አይደለም"*** መባሉ፤ ማንን ያሳምናል ተብሎ ነው?"ፀረ-ህዝብ፣ፀረ-ልማት፣ህገ-መንግስት አፍራሽ፣ ዋጋቸውን ያገኛሉ..."ወዘተ ምን የሚሉት ሀሳብ ነው?መንግስት እነሱን የማሰር ሀሳቡ ከሌለው ከአገር ከወጡ በሁዋላ ቢሯቸውን ምን አስበረበረው? ኮምፒተሮቻቸውንስ ምን አስወሰደው? እንዴ የኢህአዴግ የመድብለ ፓርቲ ምህዳርና የፕሬስ ነፃነት ወሰኑና ጥጉ የት ድረስ እንደሆነ አለም ያወቀው ፀሀይ የሞቀው ጉዳይኮ ነው።ጠንካራ ፓርቲና ጠንካራ ፕሬስ ሆኖ ብቅ ማለት ምን ሊያስከትል እንደሚችል ማን ያልገባው አለ ተብሎ ነው ዛሬ ስለፖለቲካ ምህዳርና ስለ ፕሬስ ነፃነት እንንገራችሁ የምንባለው? ለማያውቁሽ ታጠኚ አሉ መምሬ አከለ?

ይህንን ሁሉ ሀቅ አፍነው፡-"ኢትዮጵያ በዲሞክራሲ ማእበል መጠመቋን አቶ መለስ ገለፁ" የሚሉን እነ ኢቲቪና አዲስ ዘመንስ፤የግሉን ፕሬስ ከሙያና ከዲሞክራሲያዊነት አኳያ የሚዘልፉበትን ዕውቀትና ሞራል ከየት አገኙት? ነገሩ ለሃሳብ አዘል ትችት እንጅ ለዘለፋና ለክስ ምን ዕውቀት ያስፈልገዋል?

ከሁሉም በጣም የሚገርመው ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰሞኑን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ፤ኢቲቪ በግሉ ፕሬስ ላይ ስለከፈተው ዘመቻ ለቀረበላቸው ጥያቄ፤ "...ፕሮግራሙን ባላየውም ከሰዎች እንደሰማሁት በጣም ጥሩ ዶክመንተሪ እንደሆነ ተረድቻለሁ" ማለታቸው ነው። አላዩትም፤ከሰዎች ነው የሰሙት። ያን ቀረርቶ "ጥሩ ፕሮግራም ነው"ብለው የሚነግሯቸው እነማን ናቸው ? ብለን አንጠይቅም። ዞምቢዎቹ መሆናቸውን እናውቀዋለንና።

" ያው እንደልማዷ- አስታጥቃ ላከችው፣

እሱም መተኮስ ነው- እሷ በል ካለችው "

ስለፅሁፉ ያለዎትን አስተያየት በ dhabtewold@gmail.com ለፀሀፊው መላክ ይችላሉ።